የሰ/መ/ቁ. 45371

የካቲት 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**:- መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**:- የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቴ - ም/ሰብሣቢ ደሣለኝ ዲባባ ቀረቡ

**ተጠሪ**:- 1. አቶ ማሞ ተሰማ - ቀረቡ

2. አቶ ጌታቸው ይልማ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ወይንሸት ሙላት - ቀረቡ

**ብ ይ ን**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪች ለፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች ማሕበር ውስጥ አባል መሆናቸውን ገልፀው ማሕበሩ ያለአግባብ ለ6 ወራት ከማህበሩ ስላገዳቸው ይኸው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ የተለያዩ መቃወሚያዎችና በአማራጭ መልስ የሰጠ ሲሆን በመልሱም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎቹ ከማሕበሩ የታገዱት የማሕበሩን ገንዘብ ገቢ አላደርግም በማለታቸው እና ሦስተኛ ተጠሪ ደግሞ በስብሰባ ላይ ፀያፍ ንግግር በማናገራቸው በመሆኑ እገዳው ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ያቀረባቸውን መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎቹ ጥፋት ለመፈፀማቸው በቂ ማስረጃ አልቀረበም በሚል እግዱ ተነስቶ ከሙሉ መብታቸው ጋር ወደ ማሕበሩ አባልነት እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው በዋናነት ተጠሪዎች የታገዱት በማሕበሩ የመጨረሻ የስልጣን አካል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ተጠሪዎችም የታገዱት በጥፋታቸው በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ከማህበሩ ያለአግባብ ያገዳቸው መሆኑን ጠቀሰው ይኸው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ነው የጠየቁት፡፡ አመልካች ደግሞ በተጠሪዎችን ከማህበሩ ማገዱን ሳይክድ እርምጃው ተገቢ ነው በማለት ነው የሚከራከረው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት ሊመለስ የሚገባው ተጠሪዎቹ ለ6 ወር ሊታገዱ ይገባል አይገባም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነውም ተጠሪዎች ጥፋት አጥፍተዋል በሚል ከማህበሩ የታገዱት ከጥር 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ የታገዱትም ለ6 ወራት ስለመሆኑ ተጠሪዎች በክሳቸውም የጠቀሱት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በክርክር ላይ እያለ ግን ተጠሪዎቹ ከማህበሩ የታገዱበት የጊዜ ገደብ አብቅቷል፡፡ ጊዜው ካበቃ ደግሞ እገዳው አግባብ ነው አይደለም የሚለው ነጥብ መወሰኑ ውጤት የሚኖረው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ አብቅቷልና ነው፡፡ ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን ፍ/ቤቱ በቂ በሆነ ማስረጃ የተገነዘበው ከሆነ ክሱን ሊዘጋው እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የእገዳውን ግዜ በመጠናቀቁና የክሱም ምክንያት በዚሁ ስለተቋረጠ ክርክሩ ሊቀጥል የሚገባበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ሊታገዱ ይገባል አይገባም የሚለውን ፍሬ ጉዳይ መወሰን ሳያስፈልግ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ስለተቋረጠ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 መሰረት ተዘግቷል፡፡

መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ